# ከሰው እና ከወርቅ የቱ ይበልጣል?

**Seyoum Teshome**

**Development, Economy**

ሚያዝያ **30, 2018 0 Minutes**

በኦሮሚያ ክልል ጉጂ ዞን ለገ-ደንቢ (Lege Dembi) እና ሳካሮ (Sakaro) በሚባሉ አከባቢዎች ከሚገኙት የሜድሮክ (MIDROC) ወርቅ ማውጫዎች የሚወጣው መርዛማ የሆነ ኬሚካል በአከባቢው ነዋሪዎች፣ እንስሳት እና ስነ-ምህዳር ላይ የከፋ ጉዳት እያስከተለ ይገኛል፡፡



ፎቶ፡- በመንገዱ በስተግራ ያለው ውሃ በኬሚካል የተበከለ ነው!     Photo Credit ©Gaurdian

የአዶላ ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተር የሆኑት ዶ/ር ቡሻ ባላኮ ለ OBN በሰጡት አስተያየት ከፋብሪካው የሚወጣው መርዛማ ኬሚካል በሰውና እንስሳት ፅንስና አወላለድ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሏል፡፡ ለምሳሌ ባሳለፍነው የፈረንጆች አመት (2017) ብቻ ከ 157 በላይ ህፃናት ገና በእናታቸው ማህፀን ውስጥ (በፅንስ) እንዳሉ መሞታቸውን ዳይሬክተሩ ገልፀዋል፡፡ በተለይ የአከባቢው እናቶች ከፅንስ ማስወረድ ጋር ተያይዞ ባጋጠማቸው የስነ-ልቦና ችግር ምክንያት እስከሚወልዱ ድረስ እርግዝናቸውን እንደሚደብቁ ተገልጿል፡፡



FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF MINES, PETROLEUM AND NATURAL GAS

Midroc Gold Mine PLC
Sub city Nefas Silk Lafto,
Tel.: +251 113 728234 / +251 911 207236
Addis Ababa

Subject: - Renewal of Large Scale Gold Mining License

It is to be recalled that Midroc Gold Mine PLC has applied for the renewal of a Large Scale Gold Mining License that has been conducted at Lege Dembi Locality, Odo Shakiso Woreda, Guji Zone in Oromia National Regional State.

Accordingly, your application has been carefully evaluated and found to satisfy the requirements of the Law; hence, the Ministry of Mines, Petroleum & Natural Gas hereby approves the renewal of Large Scale Gold Mining License (License No. MOM/LSML/N/A) to Midroc Gold Mine PLC in accordance with Article 27 sub article 2 and 3 of the Mining Operations Proclamation No. 678/2010 (as amended by Proclamation No. 816/2013); consequently, the Mining Renewal Period shall be valid for 10 (ten) years starting from this day of March 29, 2018.

Therefore, you are required to resume the mining operation and diligently pursue the implementation of the work program submitted for the renewal period, as per the feasibility study, within sixty days (60) from the effective date; and comply with obligations provided for this renewal license, in the renewal agreement, the Mining Operations Proclamation, Income Tax Proclamation, Mining Regulation, Directives and applicable laws. Additionally, you are required to comply with Environmental standards and expected to take remedial measures on time according to the compliance Audit report.

To this effect, the Water, Mines and Energy Bureau of the Oromia National Regional State is notified, by a copy of this letter and the Renewal Agreement 39 (thirty nine) pages, of the approval of this Mining Renewal License, and so, you are required to pay annually in advance land rentals of the license area as per the applicable laws of the Regional State; and the Regional State is hereby requested to render all the necessary assistance for smooth operation of the mining activity. This agreement document shall remain confidential except for Government use.

Sincerely,

Motuma Mekassa
Minister

CC:
Water, Mines and Energy Bureau of the Oromia National Regional State

Photo Credit: ©Social Media

በተመሣሣይ አንድ በቢቢሲ የቀረበ ጥናታዊ ዘገባ የተጠቀሰው መርዜማ ኬሚካል በቤት እንስሳት ፅንስና አወላለድ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ መሆኑን ገልጿል፡፡ ይህ የሜድሮክ የወርቅ ማውጫ ባለፈው አመት ኮንትራቱ የተጠናቀቀ ቢሆንም ሰሞኑን ውሉን በአስር (10) ዓመት እንዲያራዝም ተፈቅዶለታል፡፡ በመሆኑም በአከባቢው ማህብረሰብ፣ እንስሳትና ስነ-ምህዳር ላይ ሲደርስ የነበረው ጉዳት ለአስር አመት እንዲቀጥል ተወስኗል፡፡ በዛሬው ዕለት የአከባቢው ነዋሪዎች ይህን ሃላፊነት የጎደለው ውሳኔ በመቃውም የተቃውሞ ሰልፍ አድርገዋል፡፡ ጥያቄው በአስቸኳይ ምላሽ የማያገኝ ከሆነ የነዋሪዎቹ ተቃውሞ የሚቀጥል ይሆናል፡፡



የሜድሮክ (MIDROC) ወርቅ ማውጫዎች ኮንትራት መራዘምን በመቃወም የተካሄደ የተቃውሞ ሰልፍ
Photo Credit @ Social Media

የልማት፥ ዴሞክራሲ፥ ሀገር ሆነ መንግስት ትርጉምና ፋይዳ ሰውና ሰው ብቻ ነው፡፡ የሰው ልጅን ሰብዓዊ

መብትና ክብር የሚፃረር ተቋም ሆነ አሰራር ትርጉም-አልባ፥ ፋይዳ-ቢስ ነው፡፡ የወርቅ ማዕድኑን ለማውጣት ጥቅም ላይ የሚውለው መርዛማ ኬሚካል በለገ-ደንቢ እና ሳካሮ የሚገኙ እናቶችን ፅንስ እያስወረደ ነው፡፡ በእርግጥ ወርቅ ውድ ማዕድን ነው! ነገር ግን፣ ምንም ያህል ውድ ቢሆን ከሰው ልጅ ህይወት አይበልጥም፡፡ ያለ ምንም ለውጥ የድርጅቱን ኮንትራት በአስር አመት እንዲራዘም የፈቀደው የመንግስት አካል ከሰው ይልቅ ለወርቅ ዋጋ መስጠቱን በግልፅ ይጠቁማል፡፡ ሆኖም ግን፣ ለአከባቢው ወላጆች ልጆቻቸው ከወርቅ በላይ ውድ ናቸው፡፡ በመሆኑም በኬሚካሉ ምክንያት የእናቶች መሃፀን ከሚዘጋ ወርቅ ማውጫው ቢዘጋ ይመርጣሉ፡፡